# ሰው ተቆለቆለ !!

(መይሳው፡ ከምድረ፡ ስዊድን)

ወንድምህን፣ ካማኻው ፣

ስጋውን፡ ቦጭቀህ ፣ አንተ፡ ከበላኸው ፣

ሠላሙን፡ ነስተኸው ፣ ምን ፡ ብታሳንሰው ፣

መገለጡ፡ አይቀርም ፣ ዕውነቱ ፣ መውጣቱ ፣

ክፋትህ፡ ቅናቱ ፣ ፍንትው፡ ማለቱ ፣

አንጀቱን፡ አቁስለህ ፣ እሱን፡ ያሳዘንከው ፣

ሶከሳካው ፡መቀስ አፍ ፣ አንተ፡ ማን፡ ሆነህ፡ ነው?

የጠጣኸው፡ ጽዋ ፣ ለኔ የጎፈነነ ፣

የሰራሃው፡ በደል ፣ ሰውን ያሳዘነ ፣

የሄድክበት፡ መንገድ ፣ ሰው እየነበዘ ፣

ሰው፡ ተቆለቆለ ፣ ሰው እየሸለገ ፣

ወንድሙን፡ በድሎ ፣ ቅስም እየሰበረ ፣

ወሬ፡ እያጣፈጠ ፣ ሌላው እያረረ ፣

በሰው፡ የቆመረ ፣ ልቡና የሰበረ ፣

በቁሙ፡ የሞተ ፣ ተምሮ ያልተማረ ፣

ጎብጦ፡ የተሰራ ፣ የምድሩ ቀልባጤ፣

በሕዝብ፡ የተጠላ ፣ የምድራችን ፡ ውግዝ ፣

የጉም፡ ጅብ ፡አጅሬ ፣ ለሰው የማያዝን ፣

የመጭውን ፡ግዜ ፣ የማያመዛዝን ፣

ሰብዓዊነት፡ የለው ፣ ዕዝነ ልቡና ፣

የወሬ ጋሙዳ ፣  ስጋ ቦጨቀና፣

ወንድሙን ኣወከ ፣ ህሊና ፣ አጣና፣

ሰው ፡መሳይ፡ በሸንጎ ፣ የተንሶለሰለ ፣

የሰው ስጋ፡ ምሳው ፣ ለወገኑ ያላለ።

2020-06-22